# የአምልኮ ስብሰባ አመራር

በፓስተር ዶክተር ተስፋ ወርቅነህ

© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

# የአምልኮ ስብሰባ አመራር
## በፓስተር ዶክተር ተስፋ ወርቅነህ

*መግቢያ*

ከመድረክ አገልግሎቶች አንዱ የአምልኮ ስብሰባዎችን (የጉባኤ መዝሙር) መምራት ነው። በአምልኮ ስብሰባዎቻችን የምንዘምራቸው መዝሙሮች አእምሮአችን ከዚህ ሕይወት ልዩ ልዩ ጣጣና የሕይወት ውጣ ውረድ ነጻ እንዲሆን፣ መንፈሳችንም ከፍ እንዲልና በአምልኮ መንፈስ ወደ ሰማይ እንድናርግና ወደ እግዚአብሔር ሕልውና እንድንገባ የሚያስችሉ ናቸው።መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ ነው። የሚመለከውም በእውነትና በመንፈስ ነው (ዮሐንስ 4፥23) ይላል።

ወደ እግዚአብሔር ዙፋን መንፈሳችን አርጎ በህልውናው ፊት መገኘት የምንችለው በአንድ ጊዜ (ፈጣን) በሆነ ሁኔታ አይደለም። የሰው አእምሮና መንፈስ ከዚህ ዓለም የኑሮ ጣጣና ውጣ ውረድ ለመነሳት ጊዜ ያስፈልገዋል። ለዚህ ነው አምልኮ ቅጽበታዊ ጉዳይ ሳይሆን ግስጋሴ ወይም ንቅናቄና እርምጃ የሆነው። በአምልኮ ውስጥ ስንቆይ ቀስ በቀስ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን መቅረብ እንችላለን። በመጀመሪያ ከምንገኝበት ሁኔታ (ከውጪ)፣ ቀስ በቀስ ወደ ቅጥሩ፣ ከቅጥሩ ወደ መቅደሱ፣ ከመቅደሱ ደግሞ ወደ ቅድስት በመጨረሻም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ማለትም ፍጹም የሆነው የእርሱ ህልውና (His presence) ወደሚሰማን ቦታ እንደርሳለን። በጉባኤ የምንዘምራቸው የአምልኮ መዝሙሮች ይህንን እንቅስቃሴ የምናደርግቻቸውና እግዚአብሔርን ከፍ የምናደርግባቸው ናቸው።

አንድ የሰልፍ ወይም የሙዚቃ ጉድን በኅብረት በመምረትና ሰዎችን በአውራ ጐዳና ላይ ለቅቆ እንደፈለጉት እንዲመላለሱ በማድረግ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። የሙዚቃ ባንድ በሰልፍ ለመምራት ሁሉንም በአንድ አላማ ተመሳሳይ በሆነ እርምጃ አንድ አይነት ዜማበሕብረት በመጫወት እንዲጓዙ ማድረግን ይጠይቃል። ስለሆነም ሰዎችን በአውራ ጎዳና ላይ ለቅቆ እንደፈለጉት እንዲመላለሱ ከማድረግ ይልቅ የሙዚቃ ባንድ መምራቱ የተለየና የጠለቀ የአመራር ችሎታና ዲሲፕሊን ይጠይቃል።

የጉባኤ መዝሙር በምንመራበት ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ በዓላማና በአንድነት አብሮ በምሥጋና ወደ እግዚአብሔር ዙፋን እንዲጓዝ ማድረጋችን ነው። ስለዚህ ሕዝብ ስብስቦ ያለ ስርአት በማንጫጫትና፤ በስርዓትና በአንድነት የአምልኮ ጉዞ የሚያደርግን ሕዝብ በመምራት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ማንም ሰው በጉባኤ መካከል ቆሞ መዝሙር ሊመራ ይችል ይሆናል። ነገር ግን እውነተኛ የአምልኮ ሰራዊትን ለመምራት ትልቅ ችሎታ ይጠይቃል። ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ሌሎችም የእግዚአብሔር አገልጋዮች ልምምዳቸው በጨመረ ቁጥር የመሰበክ የማስተማርና የማገልገል ችሎታቸው የሚዳብረውን ያህል የአምልኮ ስብሰባ መሪዎችም ከትምህርት፣ ከጊዜና ከተለያየ ልምምድ የተነሳ በአገልግሎታቸው ማደግ ይችላሉ።

እረኛ የሌለው መንጋ ወዲህና ወዲያ እንደሚቅበዘበዝ ሁሉ የስብሰባ መሪ የሌለበት ጉባኤም እንደዚሁ ነው። ለአንድ ስብሰባ አንድ አይነት ትኩረት ( focus) ሊሰጠው የሚችለው በአምልኮ ስብሰባ መሪው ነው። የስብሰባውም ስኬት የሚለካው በአምልኮ ስብሰባ መሪው ነው። የአምልኮ ስብሰባ መሪ የአንድን ስብሰባ ጥራት (quality) ሊወስን ይችላል። ማለትም የስብሰባ መሪው የስብሰባውን መንፈስ ሊያነሳሳና ከፍ ሊያደርግ ወይም ዝቅ ሊያደርግና ሊገድል ይችላል። እንደዚሁም ለአምልኮየተሰበሰበውን ምእመን በማሰልቸት ሊያስተኛና የጉባኤውንም መንፈስ ገድሎ የሰባኪውን መልእክት በሚገባ እንዳይሰሙ ሊያደርግ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ጉባኤው ለቃሉና ለመልእክቱ ልቡ እንዲነሳሳና በጉጉት እንዲጠብቅ ሊያደርግ የሚችለውም ይኸው የስብሰባው መሪ ነው። የስብሰባው መሪ የጉባዔውን ሁኔታ (mood) ማበላሻት ወይም ማሳመር ይችላል።

ስለዚህ የአምልኮ ስብሰባ መሪዎች ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። የስብሰባ መሪዎች በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ጉባኤ ፊት በሚቆሙበት ጊዜ ይህንን ኃላፊነት በሚገባ መረዳት ይኖርባቸዋል። ስልጠና ስብሰባም አስፈላጊ ሆኖ የተገኘውም በዚሁ ምክንያት ነው።

© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS   WWW.ECFCHOUSTON.ORG

## አምልኮ ምንድነው?

«አምልኮ» የሚለው የእንግሊዘኛው ቃል "Worship" የተገኘው "Worthscipe" ወይም " Worth Ship " ከሚለው የአንግሎ ሳክሶን ቃል ነው። ይህም አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ምን ዓይነት ቦታና ምን ዓይነት ከፍተኛ ዋጋ እንዳለው የሚገልጽ ነው። ለአንድ ሰው የምንሰጠው ዋጋ ከፍተኛ ሲሆን ለዚያ ሰው ያለንን አክብሮትና አድናቆት የሚገልጽ ድርጊት እናደርጋለን። «ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ ቁርባን ያዙ ወደ አደባባዩቹም ግቡ።» (መዝሙር 96፥8)

ሰው የተፈጠረበት ዋና ዓላማ እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር ነው። (መዝሙር 96፥6-7) ሰው ይህንን የተፈጠረበትን ዋና ዓላማ ሲተውና ሲረሳ የተለያዩ ችግሮች ውስጥ ይወድቃል። ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ የሚገባውን አምልኮ ያላደረጉትን ሰዎች፥ እግዚአብሔር ለማይረባ አእምሮ እንደተዋቸውና የተለያዩ ችግር ውስጥ እንደገቡ በሰፊው በመዘርዘር ያስጠነቅቃል። (ሮሜ 1፥18-32) በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር በእውነትና በመንፈስ የሚያመልኩትን እንደሚፈልግ ቃሉ ያስተምረናል። (ዮሐንስ 4፥23) ሰው የተፈጠረው ፈጣሪውን የማምለክ ፍላጐት በውስጡ ኖሮ ነው። የመብላትና የመጠጣት ፍላጐት እንዳለው ሁሉ አምላኩን የማምለክ ፍላጐት በውስጡ አለ።

ብሉይ ኪዳን የሚሰጠው ትርጉም

«አምልኮ» ለሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱ ሦስት የዕብራይስጥ ቃላት አሉ። እነርሱም፥

- ሀ) SCHACHAH (Shaw – KHAW) በብሉይ ኪዳን አምልኮ ለሚለው ቃል በብዛት የተጠቀሰው ይህ ቃል ሲሆን ትርጉሙ «ማጐንበስ፤ ዝቅ ማለትና መስገድ» ማለት ነው።
- ለ) ABED ( A – Bed) ትርጉሙ «ማገልገል» ማለት ነው።
- ሐ) YARE SEGID የሚሉት ቃሎች ደግሞ የአክብሮት ፍርሀትን፣ አክብሮትንና ጐንበስ ብሎ መስገድን (Reverence, Respect, Awe) የሚያሳዩ ናቸው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው ትርጉም

በአዲስ ኪዳን ውስጥም እንደዚሁ «አምልኮ» የሚለው ቃል የተተረጐመበት ሦስት የግሪክ ቃላት አሉ። እነርሱም፥

- ሀ) PROSKUNEO (Pros-Koo-Neh-o) ትርጉም ቀርቦ ዝቅ ብሎ እጅ መሣምን የሚያሳይ ነው። ይህም ልክ ውሻ የጌታውን እጅ እንደሚልስ ማለት ነው።
- ለ) LATREUO (La-Trueo) ትርጉሙ ማገልገል ማለት ነው።
- ሐ) SEBOMAI የአክብሮት ፍርሃት (ቅዱስ ፍርሀት) ማለት ነው። (Reverence)

በእነዚህ ትርጉሞች መሠረት አምልኮ ስለእግዚአብሔር ያለን አመለካከትና አስተሳሰብ ሲሆን ይህም ለእርሱ ያለን አመለካከትና አስተሳሰብ በድርጊታችን ሲገለጽና ስናገለግለው ነው።

## አምልኮ የሚከተሉት ሶስት እቅጣጫዎች አሉት።

ሀ) **ወደ ላይ (ወደ ሰማይ) የሚያመለክት** (the vertical aspect of worship)

በአምልኮ የምናጠፋው ጊዜና ኃይል እግዚአብሔርን ለማገልገልና ለመባረክ ነው። በምናመልክበት ጊዜ መባረክ ብንችልም የአምልኮ ዓላማ በኛ መባረክ ላይ ያተኰረ መሆን የለበትም። የአምልኮ ዋና ዓላማ እግዚአብሔርን ለመባረክ፣ ለማመስገንና ከፍ ከፍ ለማድረግ ነው። ስለሆነም ጥሩ የአምልኮ ጊዜ ነበረ ማለት የሚቻለው እኛ

© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

ጥሩ ጊዜ ስለነበረንና ስለተደሰትን ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በእኛ አምልኮ ደስ ያለው ሲሆን ብቻ ነው።

**ለ) ወደ ጐንና ወደ ጐን የሚመለከት** (the Horizontal aspect of Worship)

አማኞች በአንድ ላይ ሆነው በኅብረት በሚያመልኩበት ጊዜ በአማኞች መካከል ያለው አንድነት እንዲጠናከር ይረዳል። እያንዳንዱ አማኝ በአማኝ ወገኖቹ ፊት በጌታ ያለውን እምነቱንና ፍቅሩንም ለመግለጽ እድል ያገኛል። አብረው በኅብረት እግዚአብሔርን በማምለካቸውና ከፍ ከፍ በማድረጋቸው የሰዎች ልብ ለቃሉ የተዘጋጀ እንዲሆን ያደርጋል።

**ሐ) ወደ ራስ ሕይወት ማለት ወደ ውስጥ የሚመለከት** (the Inward aspect of Worship)

አንድ አማኝ በሚያመልክበት ጊዜ እግዚአብሔርን ተፈትቶ በነፃነት ለማመስገን ይችላል። በውስጡ ያለውን የእግዚአብሔር እውነት እንዲያድግና እንዲበለጽግ ያደርጋል። የእግዚአብሔር ኅልውናም ስለሚሰማው በቅዱስ አምላክ ፊት በቅድስና መመላለስ እንደሚገባው ይማራል። አምልኮ እግዚአብሔር በእርሱ ሕይወትና በጉባዔውም መካከል ለሚያደርጋቸው ነገሮች ዝግጁ እንዲሆን ያደርገዋል።

## የአምልኮ ስብሰባ መሪ

የአምልኮ ስብሰባ መሪ ዋና ሥራ ሕዝቡን በአምልኰና በምስጋና መዝሙሮች ልቡን ወደ እግዚአብሔር እንዲያነሳ በማድረግ ወደስብሰባው የመጡበት ዋና ዓላማ እንዲሟላ ማድረግ ነው። ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡት እግዚአብሔርን ለማግኘት ነው። የአምልኮ ስብሰባዎች ዓላማ ሰዎች ከፈጣሪያቸው ጋር ግኑኝነትና ኅብረትእንዲያደርጉ ማድረግ ነው። ስለዚህ የአንድ የአምልኮ ስብሰባ ስኬት በዕለቱ ጉባዔውን በአምልኮ የሚመራው መሪ ላይ ያረፈ ነው። ከዚህ የተነሳ የአምልኰ ስብሰባ መሪነት አገልግሎት እንደቀላል ነገር መታየት የለበትም።

## ለአምልኮ ስብሰባ መሪነት የሚያበቁ ነገሮች (Qualifications)

**ሀ) የደህንነት ልምምድ**

በቤተክርስቲያን ውስጥ የምንሰጣቸው ማንኛውም ዓይነት አገልግሎቶች በሙሉ ከደህንነት በኋላ የሚመጡ ናቸው። የቤተ ክርስቲያን የመድረክ አገልግሎቶች በዓለም ካለው የመድረክ አገልግሎቶች የተለዩ ናቸው።

በዓለም ላይ በመድረክ የሚቀርቡ ነገሮች ሁሉ በመጀመሪያ የሚጠይቁት ችሎታን ነው። በቤተ ክርስቲያን የመድረክ አገልግሎት ውስጥ ግን ችሎታና ተሰጥኦ ቦታ ቢኖራቸውም ዋና ነገሮች አይደሉም። የአንድ ሰው ከመድረክ ቆሞ ለመዘመርም ሆነ ለማዘመር ያለው ችሎታም ሆነ ድምጹ ብቻ የአምልኮ መሪ ለመሆን በቂ አያደርጉትም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ማናቸውንም ዓይነት አገልግሎቶች የሚሰጡ ሰዎች ሁሉ የግል የደሕንነት ልምምድ ያገኙ መሆን አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን እንኳን በመድረክ ላይ የሚደረጉ አገልግሎቶች ቀርቶ ከመድረክ ውጪ የሚሰጡ አገልግሎቶች ሁሉ የደህንነት ልምምድ ባላቸው ሰዎች ብቻ እንዲካሄዱ የማድረግ ግዴታ አለባት።

**ለ) የተመሰከረለት መንፈሳዊ ሕይወት (Proven Spiritual Walk)**

ከመዳን ቀጥሎ ከአንድ የስብሰባ መሪ የተረጋገጠና የተመሰከረለት መንፈሳዊ ሕይወት ይጠበቅበታል። የመድረክ ላይ አገልግሎቶች ሁሉ ችሎታና ስጦታ ብቻ ሳይሆን ምስክርነት ያለው መንፈሳዊ ሕይወትን ይጠይቃሉ። በመድረክ ላይ የሚቆሙ ሰዎች ልክ በማይክሮስኮፕ እንደሚታዩ ነገሮች ናቸው። የሚናገሩትና የሚዘመሩት ብቻ ሳይሆን የየእለቱ አኗኗራቸውና ሕይወታቸው ጭምር ነው። አገልጋዮች የሚታየው በሕይወታቸውና በሚሰጡት አገልግሎት (መስበክ፣ መዘመር፣ ሙዚቃ መጫወት ... ወዘተ) መካከል ቅራኔ ካለ በአገልግሎታቸው የሚነካና የሚመሰጥ አይኖርም። ስለዚህ ምንም እንኳን መላእክት መሆን ባይጠበቅባቸውም አገልጋዮች ምስክርነታቸው የተበላሸ እንዳይሆን ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚጠነቀቁ ሰዎች ሊሆኑ ይገባል።



© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

## ሐ) አምላኪ መሆን

የአምልኮ ስብሰባ መሪ ከሁሉ አስቀድሞ እራሱ አምላኪ መሆን አለበት። ራሱ አምላኪ ያልሆነ መሪ ሌሎችን በአምልኮ ለመምራት ቢሞክር ግብዝነት ይሆናል። አንዳንድ ክርስቲያኖች ስለሙዚቃ ችሎታቸው፣ ስለ ድምጻቸው ውብትና የመዝሙር ችሎታ ወይም ከዚህ ለተለዩ ሌሎች አላማዎች የስብሰባ መሪዎች ለመሆን ይወዳሉ። ቤተ ክርስቲያንም አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ለመዘመር ከአላቸው ችሎታና ስለ ድምጻቸው ጥሩነት ብቻ የአምልኮ ስብሰባ እንዲመሩ በማድረግ ትሳሳታለች።

ነገር ግን አምልኮ መምራትን ለምንም አላማ (ጥሩ/መጥፎ) በመውደድና በግል አምላኪ በመሆን መካከል ብዙ ልዩነት አለ። የአምልኮ መሪ ራሱን በመርሳት ራሱ በማምለክ ጉባኤዉን በአምልኮ መምራት አለበት። ለመሪነት ከሚያስፈልጉት ብቃቶች ውስጥ ይህ ከፍተኛ ቦታና ክብደት ሊሰጠው ይገባል። የአምልኮ ስብሰባ መሪዎችን የሚመርጠውና የሚደለድለው ክፍል የዚህን አስፈላጊንት ጠንቅቆ ማወቅ አለበት።

## መ) ከሚያገለግሉት ቤተ ክርስቲያን የአምልኮና የመዝሙር ልማድ (style) ጋር መተዋወቅ

በተለያዩ ቤተ ክርስቲያኖች የተለያዩ የአምልኮ መንገዶች (sytle) አሉ። የአምልኮ ስብሰባ መሪ መሆን የሚፈልግ ሰው ከነዚህ ሁኔታዎች ጋር የሚተዋወቅ መሆን አለበት። ለማስተማር የሚፈልገው አዲስ ነገር ቢኖር እንኳን በኃይሉና በራሱ ፍላጎት ብቻ እንደፈለገው ከማድረግና ብሎም አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ከመፍጠር በነገሩ ከእረኛውና ከቤተ ክርስቲያን መሪዎቸ ጋር አስቀድሞ መወያየት አለበት።

## ሠ) ስለ ሙዚቃ ኃሳብ ሊኖረው ይገባል

የአምልኮ ስብሰባ መሪ የሙዚቃ ችሎታ ቢኖረው የሚውደድና የሚመረጥ ነው። ነገር ግን የስብሰባ መሪ የግድ ስለሙዚቃ መጠነኛ ኃሳብ ሊኖረው ይገባል። ጉባዔውን በመዝሙር በሚመራበት ጊዜ ሙዚቃውን የመከተል ልማድ፤ በትክክለኛ ድምጽ (pitch) መጀመር፣ የሙዚቃውን (bit) መጠበቅ፣ ሙዚቃውና መዝሙሩ አብሮ ሳይሄድ ሲቀር ማወቅና አቁሞ አስተካክሎ እንደገና መጀመርን የመሳሰሉትን መሰረታዊ ነገሮች ማወቅ አለበት። ሙዚቀኛው የሚጫወተው መዝሙርና እርሱ የሚያስዘምረው መዝሙር የተለያዩ ሲሆኑ ሁሉቱ ኳሱን ወደ ተለያየ አቅጣጫ እንደሚመቱ የአንድ ቡድን ኳስ ተጫዋቾች ይሆናሉ። የዚህ አይነት ሁኔታ ሲፈጠር ጉባዔው ማንን እንደሚከተል ግራ ስለሚገባው የተዘበራረቀ ዓይነት ሁኔታ ይፈጠራል። ስለዚህ የስብሰባ መሪ የግድ የሙዚቃ ችሎታ ባይኖረውም ለሙዚቃ መጠነኛ ዝንባሌ (inclination) ሊኖረው ይገባል። ይህንን ችሎታ ለማሻሻል ከሙዚቃ ተጫዋቹ ጋር ስለ ሙዚቃ አንዳንድ መሰረታዊ ነገሮችን መወያየት ይጠቅማል። በተጨማሪም የሚቻል ቢሆን የመዝሙር ችሎታውን ለማዳበር የድምጽ አጠቃቀም ትምሕርትና ( voice lesson) ስለሙዚቃ ለማወቅ የሚረዳ ኮርስ ( music appreciation) መውሰድ የበለጠ ይጠቅማል።

## ረ) ከስብሰባው መሪ ቡድን ጋር አብሮ ወደ አንድ አቅጣጫ መጓዝ

አንዳንድ ሰዎች የግል ነገሮቻቸው ላይ ብቻ ያተኩራሉ። ከሌላ ሰው ጋር ተግባብቶ አብሮ ወደ አንድ አቅጣጫ መፍሰስ አይሆንላቸውም። የአምልኮ ስብሰባ መሪ ከሌሎቹ የአምልኮ መሪ ቡድን አባላት ጋር ( team) ማለትም ከእረኛው፣ ከመልእክት አቅራቢው፣ ... ወዘተ ጋር አብሮ መፍሰስ አለበት። በቡድን አብሮ መስራትን ካላወቀ ከጉባኤው ፊት ቆሞ መምራት የለበትም። የቡድኑ ዋና ተግባር ሁሉም ኳሱን ወደ አንድ አቅጣጫ እንዲመቱ ነው።

## ሰ) ጥሩ አመለካከት ( attitude)

የጥሩ አመለካከትን (positive attitude) አስፈላጊነት ዘርዝሮ መጨረስ አይቻልም። መልካም ስብሰባ መሪም ሰለቤተ ክርስቲያኑ፣ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ ዶክትሪኖች፣ ስለ እረኛው፣ ስለ ሌሎቹ አገልጋዮች ሁሉ ጥሩ አመለካከት ሊኖረው ይገባል። ቤተ ክርስቲያኒቱ የምታስተምረውን ዶክትሪኖችም ሆነ አገልጋዮቹን የሚቃወምና የሚቃረን ከሆነ የመድረክ አገልግሎት ሊሰጠው አይገባም። የዚህ አይነት ሰው ከነቅራኔው ( resentment) መድረክ ላይ መቆሙ ለመንፈስ ቅዱስ አሰራርና በረከት እንቅፋት ይፈጥራል። ስለሆነም ይህንን አይነት እንቅፋት ከመፍጠር ራሱን ከመድረክ በፈቃዱ ማግለል አለበት።



© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

### ሸ) በየስብሰባዎቹ ሁሉ በታማኝነት መገኘት

የአምልኮ ስብሰባ መሪዎች እነርሱ የሚመሩትን ስብሰባዎች ብቻ ሳይሆን በሌሎችም መሪነት በሚካሄዱት ስብሰባዎች በየጊዜው በስብሰባዎች ላይ የመገኘት ኃላፊነት አለባቸው። እረኛው ወይም አገልጋዮች በየጊዜው እንዳለባቸው ሁሉ የመድረክ አገልግሎት የተሰ ጣቸውም ሰዎች ይህንኑ መፈጸም ይገባቸዋል።

### ቀ) ተገቢ አለባበስ

በመድረክ ላይ የሚቆም ሰው በጉባኤው የሚገኙ ሰዎች ሁሉ ዓይን የሚያርፍበት ነው። ስለዚህ ንጽህናውን መጠበቅና በአግባቡ መልበስ አለበት። የንጽህናና የአለባበስ ጉድለት የጉባዔውን ኃሳብ በሰበጣጠርና ማዛባት ይችላል። አለባበስ፣ የጸጉር አበጣጠርና የመሳሰሉት ነገሮች ለሰዎች የተለያየ ትርጉምና መልእክት ሊሰጡ ይችላሉ። ሰው የሚያየው የውጪውን ነው ( 1ኛ ሳሙኤል 16፤7)። ውጫዊ ሁኔታችን ለሰዎች ኃሳብ ይሰጣል አእምሮንም ይይዛል።

ለምሳሌ፥ ጸጉሩ ባይበጠር፣ የልብሱ ቀለማት አብረው ባይሄዱ ወይም የተዘበራረቁ ቢሆኑ፣ ክራቫቱ ባይስማማ፥ ሴቶች ከሆኑ ደግሞ ሰውነትን የሚያስነብብ የተጣበቀ ልብስ ቢለብሱ፣ ወይም አግባብነት የሌለውአጭር ቀሚስ ቢለብሱ የሰዎችን ኃሳብ ሊረብሽ ይችላል። ስለዚህ ይህንን በመሳሰሉ ሁኔታዎች የስብሰባ መሪ የሚሆን ሰው የተለየ ኃላፊነት እንዳለበት መዘንጋት የለበትም።

## የአምልኮ ስብሰባ መሪ ተግባር

የአምልኮ ስብሰባ መሪ ሆኖ የሚወለድ ማንም የለም። የአምልኮ ስብሰባ መሪነት ስጦታና ችሎታ ነው። ስለዚህ የአምልኮ አመራር ስጦታና ችሎታ መዳበር ማደግ ያለበት ስለሆነ ችሎታችንን ለማዳበር የምንችልበትን ጥበብ መማር ና መመሪያዎቹን ማወቅ፤ ያወቁተን ደግሞ በተግባር ላይ እያዋሉ ማደግ አስፈላጊ ነው።

የአምልኮ ስብሰባ መሪ እንደ የአምልኮ ስብሰባ መሪነቱ ሦስት ዓይነት ሥራ አለው። እነዚህም

1) የእግዚአብሔር ክብር ወደ ሕዝቡ እንዲወርድ ጉባዔውን በአምልኮ መምራት።
2) የሰዎች መንፈስ እግዚአብሔርን በክብሩ ዙፋን ላይ እንዳለ ማምለክ እንዲችል ማነቃቃትና ማንሳት፤
3) በመካከላቸው መገኘቱን ያደረገውን እግዚአብሔር ጉባዔው በነፃነትና በሐሴት እንዲያከብር ማድረግ ነው።

እነዚህን ከላይ የጠቅስናቸው ነገሮች መፈፀም እንዲችሉ የስብሰባው መሪ የሚከተሉትን ነገሮች ማደረግ አለበት።

**ሀ) ጉባኤው በመንፈስና በእውነት እንዲያመልክና ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት እንዲዘጋጅ ማድረግ**
**ለ) እያንዳንዱ ሰው የአምልኮው ተሳታፊ እንዲሆን ማደፋፈር**

በአምልኮ ጊዜ ጉባዔው የማይዘምርና የማያመልክ ከሆነ ምክንያቱ ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል።

1) **መዝሙሩ አዲስ ሲሆን -**

ሰዎች በጉባዔ የሚዘመረው መዝሙር አዲስ ከሆነባቸውና ዘምረው የተለማመዱት ካልሆነ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በተመስጦ መዘመር አይችሉም። ይህ ሲሆን በአምልኮው ሰዓት የስበሰባ መሪው ብቻውን ሶሎ መስጠት ይሆንበታል። አንድ ሰው በግል ይዘምራል ተብሎ ቢዘምር (ሶሎ ቢሰጥ) መልካም ነው። ሰው ቁጭ ብሎ ይሁን ቆሞ በማዳመጥ ይመሰጣል። ስብሰባው የአምልኮ ከሆነ ግን የአምልኮ መሪው ብቻውን ሰው የማያውቀውን መዝሙር መዘመሩ አስፈላጊ አይደለም። አዳዲስ መዝሙሮቹን መዘመር ከፈለግን የአምልኮ አጃቢዎችንና መዘምራናንን በደንብ ማስጠናት፤ ቢቻል ደግሞ በሳምንቱ ውስጥ በሚካሔዱት ትናንሽ ስብሰባዎች መዝሙሩን ማስጠናት አስፈላጊ ነው። ይህ ሳይሆን አዲስ መዝሙር በሚዘመርበት ጊዜ ጉባዔው በሙሉ ተመስጦ በማምለክ ተካፋይ መሆን አይችልም።

© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

2) **ሙዚቃው በደንብ ሳይሰማ ሲቀር ወይም ሲጮኽ**

3) **የድምፅ ማጉያው መሣሪያ ሲጮኽ**

የድምፅ ማጉያው መሣሪያ በኃይል ከጮኽና ጆሮ የሚበጥስ ድምፅ ከአሰማ ሰዎች ማምለኩን ትተው ጆሮአቸውን ስለሚይዙ ወይም ሀሳባቸው ጩኸቱ ላይ ስለሚሆን በአምልኮቱ ተሳታፊ መሆን አይችሉም።

የአምልኮ ስብሰባ መሪ እነዚህ ችግሮች እንዳይከሰቱ አስቀድሞ ሁሉ ነገር በትክክል መሥራቱን ማወቅና እርግጠኛ መሆን አለበት። በአምልኮው ጊዜ የሚከሰቱትንም ፕሮብሌሞች ወዲያው ለማስተካከል ዝግጁ መሆን አለበት። የአምልኮ ስብሰባ መሪ እነዚህን ችግሮች የሚያስወግድና ሕዝቡን የአምልኮው ተሳታፊ እንዲሆን የሚቀሰቅስ መሆን አለበት።

## የአምልኮ ስብሰባ መሪ ዝግጅት

የአምልኮ ስብሰባ መምራት የረዥምና የአጭር ጊዜ ዝግጅት ይጠይቃል። ይህም ዝግጅት መዝሙር መርጦ መድረክ ላይ ከመውጣትና ከማዘመር የበለጠ ነው።

### ሀ) የረጅም ጊዜ ዝግጅት

የረጅም ጊዜ ዝግጅት ስንል በግል ሕይወታችን ከእግዚአብሔር ጋር ስለምናሳልፈው የአምልኮና የጸሎት እንዲሁም ቃሉን የማንበብ ጊዜ መናገራችን ነው።

በተጨማሪም የአምልኮ ስብሰባ መሪ በግሉ የጾምና የፀሎት ጊዜ በማድረግ የእግዚአብሔርን ፊት መሻት አለበት ። የአምልኮ ስብሰባ መሪ ዝግጅት የሚጀምረው ስሙ ፕሮግራም ላይ ሲወጣ ብቻ መሆን የለበትም። ሁል ጊዜ ከላይ በጠቀስናቸው ጉዳዮች በግል ሕይወቱ መበርታት አለበት። ስለ አገልግሎቱና ስለሚያገለግላቸው ሰዎች በየጊዜው በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት መቅረብ አለበት። ከመድረክ ለመቆምና ጉባኤውን በሚገባ ለመምራት የሚያስችለው ኃይልና በረከት በቅድሚያ ከሚደረገው ዝግጅት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው።

በሳምንቱ ቀናት ውስጥ ከእግዚአብሔር ርቆ የሰነበተ ስብሰባ መሪ በአምልኮ ስብሰባው ቀን ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ኅልውና እንዲገቡ መምራት አይችልም።

### ለ) የአጭር ጊዜ ዝግጅት

የአጭር ጊዜ ዝግጅት የምንለው የስብሰባው መሪ ከስብሰባው በፊት የሚኖረውን የአንድ ሳምንት ጊዜ ነው። ስብሰባ እንዲመራ በሚጠየቅበት ጊዜ ሁሉ የስብሰባው መሪ ራሱንና ጉባኤውን በማሰብ በእግዚአብሔር ፊት ሊቆይ ይገባል።

### ሐ) የጸሎት ዝግጅት

በጸሎት ሳምንቱን ሁሉ ከቆየ በኋላ በስብሰባው ቀን ዋዜማ ማታና የስብሰባው እለት ስብሰባውን በማሰብ መጸለይ። ስብሰባውን ከመምራቱ ቀደም ብሎ የዚህ አይነት ሕይወት ላይ ከቆየ በሚመራበት ጊዜ የሚያደርገው የዚሁ አምልኮ ቅጥያ ይሆናል።

የዚህ አይነት ዝግጅት የሚጎድለው መሪ ከሚሰጠው ጊዜ ውስጥ አብዛኛውን የሚያጠፋው የራሱን ሕይወት ከጌታ መንፈስ ቅዱስ ጋር ለማስተካከል በሚያደርገው ጥረት ነው። መሪ ሆነው በስብሰባው ላይ የረጅም ጊዜ ጸሎት የሚያደርጉ ሰዎች ብዙ ጊዜ የዚህ አይነት በቂ የግል ዝግጅት የሚጎድላቸው ሰዎች ናቸው።

### መ) ለስብሰባው ተስማሚ የሆኑ መዝሙሮችን መምረጥ

የስብሰባው መሪ በአምልኮ ላይ በሚገኝበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ያላሰበውን መዝሙሮች ወደ



© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

አእምሮው ማምጣት ይችላል። የአምልኮ መሪው ለመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ናፍላጎት ክፍት (sensitive) መሆን አለበት። ነገር ግን የስብሰባ መሪው ለማዘመር የሚፈልጋቸውን መዝሙሮች አስቀድሞ ማሰብና መምረጥ አለበት። የሚመርጣቸው መዝሙሮች ከሰብሰባው መንፈስ ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው።

**ሠ) ከሙዚቀኛው ጋር መለማመድ**

የሚመርጣቸውን መዝሙሮች ከሚዚቀኛውና ከአጃቢ ዘማሪዎች ጋር ለአጭር ጊዜም ቢሆን መለማመድ ያስፈልጋል።

**ረ) ከፕሮጀክተር አገልጋይ ጋር ስራን ማጣጣም**

የመረጣቸውን መዝሙሮች በመዝሙር መጻሕፍት ውስጥ ከሌሉ ዝርዝሮቹን overhead projector ላይ ለሚያገለግለው ሰው መስጠትና ተዘጋጅቶ እንዲጠባበቅ ማድረግ።

**ሰ) ወደ ስብሰባው ቦታ ቀደም ብሎ መምጣት**

የስብሰባው መሪ አርፍዶ መምጣትና ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ በተዋከበ መንፈስ ጉባኤውን መምራት የለበትም። ቀደም ብሎ መምጣት ሀሳቡን ለመሰብሰብና በጸሎት መንፈስ ለመቆየት ይረዳዋል። በተጨማሪም በሰዓቱ መገኘት በምእመናኑ፣ በመጋቢው በሌሎቹም መሪዎች ዓይን አስተማማኝና ኃላፊነት ለመሸከም የሚችል መሆኑን ይገልጻል። በስራ ዓለም ማርፈድ በስራ ያለመደሰትና ያለመርካት ምልክት መሆኑ ይነገራል። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የበለጠ አጸያፊ ባህርይ ነው።

**ረ) ድምጽን ከሙዚቃ ጋር ማስማማት**

የስብሰባው መሪ አስቀድሞ የሚያስዘምራቸውን መዝሙሮች በማጥናት የድምጽ መጎርነን ወይም መስለልን የመሳሰሉትን ችግሮች ማስወገድ ይችላል።

**ሸ) ሰባኪው የሚሰብክበትን ርዕስ ማወቅ**

በሳምንቱ ውስጥ ስልክ ደውሎም ቢሆን እርሱ በሚመራበት ቀን የስብከቱ ርዕስ ምን እንደሆነ ከፓስተሩ መጠየቅ። ተከታታይ ትምህርት ከሆነና ርዕሱ የሚታወቅ ከሆነም በእለቱ የሚሰብክበትን ርዕስ ማወቁ ለአምልኮ የሚያዘምራቸውን መዝሙሮች ለመምረጥና የአምልኮው አቅጣጫ በዕለቱ ከሚሰጠው ትምህርት ጋር የተደጋገፈ እንዲሆን ለማድረግ ይረዳዋል።

**ቀ) ለማዘመር ያቀዳቸውን መዝሙሮች ለሙዚቃ ታጫዋቾች ማስታወቅ።**

**በ) የሚነበቡ ጥቅሶች ቢኖሩ አስቀድሞ ማዘጋጀት።**
በተለይም እንደገና እና የፋሲካን በዓላት በሚደረጉት ዝግጅቶች የበአሉን ምክኒያት የሚያስረዱ ጥቅሶችን አዘጋጅቶ ማንበብ ጠቃሚ ነው።

ከላይ የተዘረዘሩት የረጅምና የአጭር ጊዜ ቅድመ ዝግጅቶች ለስብሰባው መሪ አገልግሎት መሳካት በጣም አስፈላጊ ናቸው። አንድን ሰመ ጥር የጦር ጄነራል አንድ ጋዜጠኛ፣ «ጠላትን ድል ማድረግ የሚቻለው መቼ ነው?» ብሎ ጠየቃቸው። እርሳቸውም ሲመልሱለት ከጦርነቱ በፊት በሚደረገው ዝግጅት ነው» ብለው መለሱለት። የእኚህ ሰው መልስ ለማንኛውም የመድረክ አገልግሎት ሊረዳ ይችላል።

## የአምልኮ ስብሰባ አመራር አጠቃላይ መመሪያ

**ሀ) ከስብሰባው በፊት ያለውን ጊዜ በፀሎትና በዝግጅት አሳልፍ**

ስብሰባው መቼ ተጀምሮ መቼ ማለቅ እንዳለበት መመሪያ እንዲሆንህ ከፓስተሩ ጠይቀህ ተረዳ። ሌሎቹን



© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

ዝግጅቶችህን ሁሉ ከአደረግክ በኋላ በጸሎትና በጥሞና ቆይ። ልዩ ልዩ ወሬ እያወሩ አእምሮን ሳይሰበስቡ በቀጥታ ወደ መድረክ መውጣት ድርቀት ያስከትላል። ስለዚህ ከስብሰባው በፊት ያለውን ጊዜ የጸሎትና የዝግጅት አድርገው።

### ለ) ራስህን ሁን

ራስን መሆን ለማንኛውም የስብሰባ መሪ አስፈላጊ ነው። ከሌሎች ሰዎች ሕይወትና አገልግሎት ብዙ ትምሕርትና ጥበብ መቅሰም ይቻላል። ነገር ግን የስብሰባ መሪ ከሌሎች የሚያገኛቸውን ማናቸውንም ዓይነት እውቀቶች ከራሱ ማንነት (personality) ጋር አዋህዶ ለአገልግሎት በሚቀርብበት ጊዜ ፍጹም ራሱን መሆን ይገባዋል። ብዙ መሪዎች በመድረክ ላይ ራሳቸውን መሆን አይፈልጉም። ከዚህ በፊት ያዩትን ሌላ ሰው እንዳለ ሙሉ በሙሉ ኮፒ በማድረግ ይቀርባሉ። ይህ አስፈላጊ ካለመሆኑም በላይ ጉባኤውም ለይቶ ሊያውቀው ስለሚችል ጥሩ ያልሆነ ሁኔታን ይፈጥራል።

### ሐ) ሰውነትህ ዘና ይበል (be relaxed) ከፊትህም ፈገግታ ይታይ (smile)

ሰዎች አንተን በማየት አእምሮአቸውን ከችግሮቻቸው ላይ አንስተው ክርስቶስ ላይ እንዲያደርጉና እንዲያመልኩ በፊትህ ገጽታ የምትሰጠው መልእክት ጥሩ (positive) ይሁን። ፈገግ ለማለት የሚጠይቀው 14 የፊት ጡንቻዎችህን ብቻ ሲሆን ለማኩረፍ ግን 72 ጡንቻዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ ይጠይቃል። ስለዚህ ፈገግታ ለሚመለከቱህ ብቻ ሳይሆን የአንተንም የሰውነት ጡንቻዎች እንዳይደክሙ ይረዳል።

### መ) አእምሮህን በራስህ ሃሳብ አትሙላ

በጌታና በጉባኤ ፊት የቆመ የስብሰባ መሪ አስከድሞ ራሱን በጸሎት ለጌታ ከሰጠና ካስረከበ አእምሮውን ስለራሱ ሁኔታ በማሰብ ከመሙላት (self consciousness) ፈጽሞ ነጻ መሆን አለበት።

የስብሰባ መሪ፣ ሰዎች ምን ይሉኝ ይሆን? በደንብ አልመራም ይሉኝ ይሆን? ወዘተ በሚል ሀሳብ ከተሞላ ራሱ የስብሰባው ተካፋይ መሆን አይችልም። ከጉባኤው ጋር አብሮ በነጻነት የማያመልክ መሪ ጥሩ የስብሰባ መሪ ሊሆን አይችልም።

ስለ እነዚህና እንደማፈር መሸኮርመም የመሳሰሉትን ነገሮች ጌታ ከእርሱ እንዲወስድለት በጸሎት መጠየቅ ያስፈልገዋል። የስብሰባው መሪ በጉባኤውና በጌታ ፊት በሚቆምበት ጊዜ የመንፈስ ዓይኖቹን ጌታ ላይ በማድረግ ራሱን መርሳት አለበት።

### ሠ) ተረጋጋ

የስብሰባ መሪ በጉባኤው ፊት ቆሞ በሚመራበት ጊዜ ከፍላጎቱ ውጪ የሆኑ አንዳንድ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። የስብሰባው መሪ በዚህ የመረበሽ ወይም የመታወክ መንፈስ ወይም ሁኔታ ማሳየት የለበትም።

### ረ) የዓይን አጠቃቀም እወቅ

የስብሰባ መሪ የዓይን አጠቃቀም ማወቅ ይኖርበታል። አንዳንድ መሪዎች ጉባኤውን ሲመሩ አይናቸውን ከጨፈኑ በፍጹም አይገልጹም። ስለዚህም በጉባኤው ውስጥ የሚሆነውን ስለማያዩ አያውቁም አይረዱትም። ሌሎች መሪዎች ደግሞ በአምልኮ ጊዜ ሁሉ ዓይኖቻቸውን ፈጽሞ አይከድኑም። ዓይንን ሳይከድኑ ዝም ብሎ መምራት ደግሞ የራሱ የሆነ ችግር አለው። ይኸውም የመሪው ዓይን ጥቃቅን በሆኑ ነገሮች ላይ እንዲያተኮሩ ስለሚያደርግ ሃሳቡን በመበታተን ግራ ሊያጋባው ይችላል።

ዓይንን መጨፈን መሪው ሃሳቡን በጌታ ላይ እንዲያተኩር ይረዳዋል። ስለዚህ መሪው በሚመራበት ጊዜ ዓይኑን የሚጨፍንበትና የሚከድንበት ጊዜ ሊኖረው ይገባል። የስብሰባ መሪ ዓይንን መጨፈንና መክደንን ሁሉቱንም ሚ ዛናዊ በሆነ መንገድ መጠቀም አስፈላጊ ነው።

© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

### ሰ) በእለቱ ሰባኪ እንዳለ አትዘንጋ

የአምልኮ ስብሰባ መሪ ስራው ስብሰባውን መምራት ነው እንጂ መስበክ አይደለም። የስብሰባው መሪ ዋና ተግባር ጉባኤው ጌታን ማምለክ የሚችልበትን ጥሩ ሁኔታ መፍጠርና ጉባኤው ለቃሉ የተዘገጀና የለሰለሰ ልብ እንዲኖረው ማድረግ ነው።

አንዳንድ የስብሰባ መሪዎች የመስበክ ችሎታቸውን በአምልኮ አመራር ጊዜ ለማሳየት ይፈተናሉ። የመስበክ ችሎታን ለማሳየትና ማወቅ የሚገባቸው ሰዎች እንዲያውቁ ለማድረግ የሚቻልበት የተሻለ ጊዜና ቦታ አለ።

አንዳንድ መሪዎች እንዲያውም ይባስ ብለው በእያንዳንዱ መዝሙርና አዝማች ሃሳብ ላይ አንድ ሳይሆን ብዙ የተለያዩ አጫጭር ስብከቶችን ያደርጋሉ። ይህንንም በሚያደርጉበት ጊዜ ስብሰባው አንድ አላማ (focus) እንዲኖረው በማድረግ ፋንታ ብዙ የተዘበራረቀ አላማ እንዲኖረው ያደርጋሉ። በተጨማሪም ተገቢ ከሆነው ጊዜ በላይ በመውሰድ የስብከቱንና በእለቱ የታሰቡትን የሌሎች ፐሮግራሞች ጊዜ ያባክናሉ።

የፐርግራም መሪው ስራ ፕሮግራም መምራት ሲሆን መስበክ ደግሞ የሰባኪው ስራ ነው። የነዚህን ልዩነት መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው።

የስብሰባ መሪ በስብሰባው መጀመሪያ ላይ የጉባኤውን ልብ የሚያዘጋጅ ጥቅስ አንብቦ አጭር የማበረታቻ ቃል ጣል ማድረግ ይችላል። በመካከልም ላይ ቢሆን ተናገር ተናገር ከሚል ፈተና የተነሳ ሳይሆን የእግዚአብሔር መንፈስ በልቡ ውስጥ የሚያደርገው ጉባኤውን በአምልኮ የሚያበረታታ ሃሳብ ካለው መናገር ይችላል። የትንቢት ስጦታም ካለውና ትንቢት እንዲናገር የመንፈስ ቅዱስ ፍላጎት ከሆነ ያንኑ ማድረግ ይችላል። ከዚህ በተረፈ ግን የስብሰባው መሪ የቀመለትን ዓላማ አውቆ በመምራት ፋንታ ወደ ስብከት ከመግባት ፈጽሞ መቆጠብ አለበት።

### ሸ) የስብሰባውን ኃሳብ (theme) ጠብቅ

በእለቱ የተሰበከው ስብከት ወይም መንፈስ ቅዱስ ጉባኤው እንዲያተኩር ያደረገው ሃሳብ በአንድ ነገር ላይ ከሆነ ያንን ሐሳብ (theme) መጠበቅ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ስለ ንሰሃ ከሆነ በዚያው ሃሳብ ላይ (ስለ ዳግም ምጽዓት ከሆነም በዚያው ሃሳብ ላይ) መቆየት ያስፈልጋል። መንፈስ ቅዱስ የጀመረውን ሥራ ሳይጨርስ ከአንዱ ኃሳብ ወደ ሌላው መዝለል ጉባኤውን ከማደናገሩም በላይ መንፈስ ቅዱስ የጀመረውን ሥራ ማደናቀፍ ም ይሆናል።

### ቀ) የራስህን ጊዜ ለጉባኤው ሰዋ

የአምልኮ ስብሰባ መሪ በጉባኤው ፊት የሚቆመው ራሱን ብቻ ለማስደሰት አይደለም። የራሱን ስሜት ለጉባኤው ሲል መጣል አለበት። ለምሳሌ እሱን ደስ ያላለው ከሆነ ጉባኤውም እንዲደበር ማድረግ አይገባውም። ስለዚህ ለመምራት በሚወጣበትና በእግዚአብሔርና በጉባኤው ፊት በሚቆምበት ጊዜ የራሱን ፍላጎትና ስሜት ለመንፈስ ቅዱስና ለጉባኤው ፍላጎት ተገዢ ማድረግ አለበት።

### በ) የግል መዝሙር (solo) ከመስጠት ተቆጠብ

የአምልኮ ስብሰባ መሪ መዝሙር ሲመርጥ ጉባኤው የሚያውቀውን መዝሙር መምረጥ አለበት። ጉባኤውን አ ዲስ መዝሙር ለማስዘመር ከፈለገ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል። ይኸውም አዲስ መዝሙር በ overhead projector እንዲዘጋጅና ጉባኤው እያየ እንዲያጠና ማድረግ ይኖርበታል።

ነገር ግን አንዳንድ መሪዎች ይህንን ሁሉ ችላ በማለት እነርሱ ብቻ የሚያውቁትን መዝሙር እየዘመሩ ብቻቸውን ያንጎራጉራሉ። ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ ስብሰባውን እየመሩ ሳይሆን solo እየሰጡ መሆኑን አያስተውሉም።

© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

### ተ) ያለማቋረጥ ከተመለከ በኋላ ጉባዔው ፀጥ እንዲል አድርግ

ያለማቋረጥ ከተመለከ በኋላ ፀጥ ሲባል እግዚአብሔር ለሰዎች ልብ ይናገራል። ሰዎችም ነፍሳቸው በፀጥታ ከአምላኳ ጋር እንድትነጋገር ጊዜ ታገኛለች። የፀጋ ስጦታዎችም በዚህ ጊዜ መሥራት ይችላሉ።

### ቸ) በእለቱ መደረግ ያለባቸውን ነገሮች አትርሳ

በአንዳንድ የአምልኮ ስብሰባዎች በተለይም በእሁድ ጠዋት የአምልኮ ጊዜ ከስብከት ሌላ መደረግ የሚገባቸው ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ይኖራሉ። ለምሳሌ፥ እንግዳ ማስተዋወቅ፣ ማስታወቂያ ማድረግ፣ መባና አስራት መሰብሰብ፣ ሕጻናትና ወጣቶች ወደ ሰንበት ትምሕርት እንዲሄዱ ማሰናበት፣ መዘምራን እንዲዘምሩ ማድረግ የመሳሰሉት ይገኙበታል።

እነዚህን ሁሉ ማስታወስ ካስቸገረው የፕሮገራሙ መሪ በማስታወሻ መያዝ ይኖርበታል። የዕለቱን ፕሮገራሞች በመርሳት ከጉባኤው መካከል ሌላ ሰው እንዲያስታውሰው ሲደረግ «ይቅርታ ረሳሁ» ማለትን ልማድ ማድረግ አግባብ ያልሆነና ሊወገድም የሚገባው ነገር ነው።

### ኀ) የማይክሮፎን አጠቃቀምን እወቅ

የማይክሮፎንን አጠቃቀም ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። የመሪው ድምጽ ከጉባኤው ድምጽ ከሚገባው በላይ ሳይጎላና ሳይጮህ አብሮ እንዲሄድ ለማድረግ የማይክሮፎንን አጠቃቀም ማወቅ የረዳል። ያለበለዚያ የመሪው ድምጽ ጩኸት የጉባኤው ድምጽ እንዳይሰማ ስለሚደመስሰው ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የመሪው የግል መዝሙር (solo) ብቻ ነው የሚሰማው።

### ነ) ምሳሌ በመሆን ምራ

የስብሰባው መሪ ለጉባኤው ምሳሌ በመሆን በቅድሚያ ራሱ አምላኪ በመሆን መምራትና ለአምልኮም ተገቢ በሆኑ የሰውነት እንቅስቃሴዎች ማሳየት አለበት።

መሪው ጉባኤውን የሚመራው፥ በማደፋፈር (Exhortation) ፣ በምሳሌነት ማለትም ቀድሞ በማሳየት እንጂ በማዘዝና በመቆጣጠር በ ( manipulation) መሆን የለበትም።

የአምልኮ መሪ በመሆንና የሙዚቃ መሪ (Conductor) በመሆን መካከል ልዩነት አለ። የአምልኮ መሪ የግድ አያዝዝም በትእዛዝም ሁሉን ነገር አያስደርግም። ጉባኤው እንዲያደርግ የሚፈልገው ነገር ካለ በምሳሌነትና በማደፋፈር ማድረግ ይኖርበታል። የጉባኤው መብት የተጠበቀ መሆኑን መዘንጋት አያስፈልግም። ስለሆነም ጉባኤው የሚጠየቀውን ለማድረግም ሆነ ላለማድረግ ፍጹም ነጻነት አለው። በማስፈራራትም ሆነ በማስገደድ የሚፈልገው ብቻ እንዲደረግ መሞከር ከፕሮግራም መሪው የሚጠበቅ አይደለም። አንዳንድ መሪዎች በማበረታታት ፋንታ ጉባኤውን በጅራፍ መግረፍ ይወዳሉ። ጉባኤው የሚፈልጉትን ካላደረገ የሚገስጹና «ታስራችኋል» በማለት የሚዘልፉም አሉ። ይህንን በቀጥታ ለመናገር ድፍረት የሌላቸው ደግሞ በጸሎት ውስጥ አድርገው ስለጉዳዩ መስበክ ወይም ለእግዚአብሔር አቤቱታ ማቅረብ ይፈልጋሉ። የአምልኮ ስብሰባ የሚመራ ሰው ከዚህ አይነት ስህተቶች መቆጠብ ይኖርበታል።

ለምሳሌ ትክክለኛ የአምልኮ ልማድ ቆሞ ማምለክ ነው። ነገር ግን ይህ ማለት ሰው ቁጭ ብሎ ሊያመልክ አይ ችልም ማለት አይደለም። አምልኮ የመንፈስ ጉዞ እንጂ የፎርሙላ ጉዳይ አይደለም። ተቀምጦም ሆነ ቆሞ ፣ እጅ ዘርግቶም ሆነ እጅ አጣጥፎ ማመለክ ይቻላል። ከጉባኤው መካከል አንዳንድ ሰዎች በተለያየ ምክንያት የሚጠየቁትን ማድረግ አይችሉም። በበሽታ፣ በእድሜ፣ በእርግዝና፣ ውፍረትን በመሳሰሉት ምክንያቶች ቆመው ማምለክ የማይችሉ ስለሚኖሩ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ጉባኤው ቆሞ እንዲያመልክ ማበረታታት ያስፈልጋል። ነገር ግን የተሰማቸውንና የሚችሉትን ቢያደርጉ ፍጹም ነጻነት እንዳላቸውእንዲያውቁ ማድረግ ተገቢ ነው።

© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

### ኘ) ሰዓት ጠብቅ

የአምልኮ መሪ ተግባሩን በተወሰነው ሰዓት መጀመር አለበት። በመንፈስ ቅዱስ የሚመራውን አምልኮ ደቂቃውና ሰከንዱ ሳይቀር አስቀድሞ ማወቅ (predicting) ያሰቸግራል። የፔንቴኮስታል ስብሰባዎች ለመንፈስ ምሪት ቦታ (sensitivity) ሊኖራቸው ይገባል።

ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የሰዎችን ጊዜና ሁኔታ ሁሉ እንደሚያውቅ መዘንጋት አያስፈልግም። ስለዚህ ስብሰባ በጊዜው ተጀምሮ በጊዜው ማለቅ አለበት። ሰዓቱ የግዴታ ሁል ጊዜ አንድ አይነት መሆን የለበትም። ነገር ግን ለጉባኤው ችግር በማይሰጥ ሁኔታመደረግ ይገባዋል። መንፈስ ቅዱስ ልዩ ጊዜ ሲሰጥና ጉባኤውም ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ሲፈለግ የመንፈስ ቅዱስ ፍላጎት ለሁሉ ሰው ግልጽ ስለሚሆን የሚያጉረመርም አይኖርም። ነገር ግን ሰዓት መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን መዘንጋት አይገባም።

### አ) እያንዳንዱን መዝሙር በማስተዋወቅ ጊዜ አታጥፋ

አምልኮ ቁርጥ ቁርጥ ሳይል ሲቀጥል (flow ሲያደርግ) ጥሩ ነው። በየመዝሙሩና በየአዝማቾች መካከል የምንዘምረው ይህንን ወይም ያኛውን ነው በማለት አምልኮውን መቆራረጥ ተገቢ አይደለም። ስለዚህ ከሙዚቃ ተጫዋቹ ጋር በምልክትም ሆነ በተለያየ መንገድ በመነጋገር አምልኮው ያለ መቆራረጥ እንዲቀጥል ማድረግ የስብሰባው መሪ ሃላፊነት ነው።

### ከ) አምልኮውን አሁንም አሁንም በጸሎት አታቋርጥ

በፔንቴኮስታል የአምልኮ ስርዓት መዝሙር ሲዘመር ቆይቶ በመካከሉ ለጥቂት ጊዜ ጉባኤው እንዲጸልይ ማድረግ የተለመደ ነው።ይህንን ማድረግ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን አምልኮ ከመጠን በላይ በጸሎት ሲቆራረጥ የአምልኮን ግስጋሴ ይገታል። የአምልኮ መዝሙር የጉባኤውን መንፈስ ወደ ላይ ከፍ ሲያደርግ ጉባኤው በጸሎት የተፈታ ይሆናል። ቢሆንም ከያንዳንዱ መዝሙርና አዝማች በኋላ ጸሎት ማስገባት አስፈላጊ አይደለም። የአምልኮ መሪውም ይህንን ከማድረግ መቆጠብ ይኖርበታል።

### ኸ) ዋናው የአምልኮ መሪ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ተገንዘብ

የስብሰባ መሪ የሆነ ሰው፣ እውነተኛውና ዋናው የአምልኮ መሪ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን መዘንጋት አይገባውም። አምልኮ መለኮታዊ ስራ ነው። ከሰዎች ልብ እውነተኛ አምልኮን ማፍለቅ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የራሱ የሆነ መለኮታዊ ፈቃድ (sovereign will) አለው። ስለሆነም ማንም በሚያዝዘው መንገድና ሁኔታ አይሰራም። እርሱ መንቀሳቀስ ካልፈለገ የስብሰባውመሪ በግድ ሊያንቀሳቅሰው አይችልም። እርሱ መስራት ያልፈለገውን መሪው ለማድረግ መድከም የለበትም።

መጽሐፍ ቅዱስ «በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም» (ዘካርያስ 4፥6) በማለት ይናገራል። የሰዎች ልብ የሚቀልጠውና የሚቀጣጠለው እርሱ ሲፈልግ ብቻ ነው። የመሪው ፋንታ መንፈስ ቅዱስ የወደደውን እንዲያደርግ ፈቃደኛ መሆን ብቻ ነው። መሪየፈለገውን ቢያደርግ ያንን ሁኔታ መፍጠር አይችልም።

### ወ) ከሚገባው በላይ መዝሙር አታብዛ

የተወሰኑ መዝሙሮችን ብቻ መምረጥና ማዘመር የጉባኤ ኃሳብ የተሰባሰበ እንዲሆን ከመርዳቱም በላይ ጉባኤው መሪውን በሚገባ እንዲከተለው ያደርጋል። ስለዚህ መዝሙሮች ከማብዛት ይልቅ መሪው መጠነኛ መዝሙሮችን ቢመርጥና ቢያስዘምር የተሻለ ነው።

### ዐ) የአምልኮ መዝመሩን ፍጥነት አትዘበራርቅ

የአምልኮ መዝሙሮች ስትመርጥ አንድ ዓይነት የሆኑትንና በተመሳሳይ ፍጥነት የሚዘመሩትን አከታትለህ አዘምር። አንዱ ፈጣን ቀጥሎ ዝቅ ያለ ሌላው ጎታታ ሲሆን የሰውም ስሜት ላይና ዝቅ ስለሚል ጥሩ አይደለም። ፈጣኖቹም ሆኑ ጐታታዎቹን አንድ ላይ በማከታተል እንጂ አንዴ ይህን አንዴ ያንን ማደረግ የሚ

© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS   WWW.ECFCHOUSTON.ORG

ያዘበራርቅ መሪ (choppy leader) ያደርጋል። የእግዚአብሔር መንፈስ ልዩ ምሪት ካልሰጠ በቀር ሁልጊዜ በፈ ጣኖች ጀምሮ ቀስ በቀስ ረጋ ወዳለው መሄድ ይመረጣል።

### ዘ) የስብሰባ አፈጻጸም እወቅ

ጥሩ የሆነ አፈጻጸም እጅግ አስፈላጊና ማንኛውም የስብሰባ መሪ በጥንቃቄ ሊያደርገው የሚገባ ነው። ሰባኪው የንስሀ ስብከት ከሰበከ የስብሰባው አፈጻጸም በዚያው ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል። ነገር ግን ይህንን ባለመከተል መሪው ስብሰባውን ከዚህ በተለየ ሁኔታ ለመዝጋት ቢፈልግ የጉባኤውን ኃሳብ ከመክፋፈሉም በላይ የስብከቱን ኃይል የሚያዳክም ይሆናል። ስለ ንስሃ ተሰብኮ ስለ መባ በመናገር መጨረስ ልክ አይደለም። ይህንን ለማድረግ የስብሰባው መሪ የእለቱን ስብከት በጥሞና ማዳመጥ ይኖርበታል።

## የአምልኮ መሪ ካልተጠነቀቀ ሊፈጽማቸው የሚችሉ ስህተቶች

### ሀ) መንፈሳዊ ዝግጅት አለማድረግ

የአምልኮ ስብሰባ መሪ ያለመንፈሳዊ ዝግጅት መድረክ ላይ ቢወጣ ከዝግጅት ጉድለቱ የተነሳ የአምልኮ ስብሰባውን ያበላሻል።

### ለ) ራሱ ከጉባኤው ጋር አብሮ አለማምለክ

የአምልኩ መሪ ምሳሌ በመሆን ራሱ ከጉባዔው ጋር አብሮ ካላመለከ ሰዎች በመመሰጥና በነፃነት እንዳያመልኩ ያግዳል። ለዚህ ነው የስብሰባ መሪው ራሱ አምላኪ መሆን የሚገባው።

### ሐ) ለእያንዳንዱ መዝሙር መግለጫ በመስጠት የአምልኮውን ጊዜ ማባከን

### መ) መስበክ

የአምልኮ ስብሰባ መሪ ሥራ ጉባዔውን በአምልኮ መምራትና ቃሉንም ለመቀበል ማዘጋጀት ነው። ለስብከት ለዕለቱ የተመደበ ሌላ ሰው አለ። ሰዎች የአምልኮውን ጊዜ መዝሙር ሊሰሙበት እንጂ ስብከት ሊሰሙበት አልተሰበሰቡም። ደግሞም በአንድ ስብሰባ ላይ ከአንድ ስብከት በቀር አያሌ ስብከት ለማድመጥ አይወዱም። ስለዚህ የአምልኮ ስብሰባ መሪ ከዚህ ስህተት መቆጠብ አለበት።

### ሠ) መፍራትና መርበትበት

የአምልኮ ስብሰባ መሪ መንፈሱን አረጋግቶ ሁሉን በመቆጣጠርጉባዔውን በአምልኮ ወደ አግዚአብሔር እንዲገሰግስ አቅጣጫ መስጠት አለበት። ከፈራና ከተርበተበተ ግን የሚጠበቅበትን ሥራ በትክክሉ መሥራት አይችልም።

አንድ ጊዜ በአንድ ስብሰባ ላይ አንድ ሰው ማይክሮፎኑን እንደያዘ ጉባዔውን ትቶ ዕቃ ለማምጣት ከስብሰባው ክፍል ወጥቶ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ መጣ። ጉባዔውም ተደናግጦ ይጠብቅ ነበር። እንዲህ የሚሆነው መርበትበትና ፍራሃት ሲኖር ብቻ ነው።

### ረ) ማስረዘም

የዕለቱ ስብሰባ አምልኩ ሊደረግበት ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ነገሮች ይካሔዱበታል። መባ ይሰበሰባል፤ የቃሉ መልእክት ይቀርባል፤ ፀሎት ለሚያስፈልጋቸው ይፀለያል። ስለዚህ ሌሎች የሚደረጉ ነገሮች እንዳሉ አለመዘንጋትና ጊዜውን ማብቃቃት ያስፈልጋል። የአምልኮው ስብሰባ ብቻ እንዲራዘም የሚያደርግ የስብሰባ መሪ በእለቱየሚደረጉትን ሌሎች ነገሮች ውጤታማ እንዳይሆኑ ያግዳል።

© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

### ሰ) ለመዝሙር ተገቢ በሆነው ድምፅ (key) አለመጀመር

እያንዳንዱ መዝሙር ሊጀመርበት የሚገባ ተገቢ ድምፅ (key) አለው። ያንን ሳይከተሉ በከፍተኛ ድምፅ መጀመር ያለበትን በዝቅታ፤ በዝቅታ ድምፅ የሚጀመረውን ከፍ ባለ ድመፅ ሲጀምሩ ጉባዔው አብሮ እየተከተለ መዘመር ያቅተዋል።

### ሸ) ጉባዔው የማያውቀውን መዝሙር ብቻ ማዘመር

ይህ ጉባዔው የአምልኮው ተሳታፊ በመሆን ፈንታ ተመልካች ብቻ እንዲሆን ይገፋፋዋል።

### ቀ) ከሙዚቀኛው ጋር አብሮ አለመሄድ

መዝሙር ሲዘምሩም ሆነ ከአንድ መዝሙር ወደ ሌላ ሲሸጋገሩ በሙዚቀኛውና በስብሰባው መሪ መካከል መግባባት መኖር አለበት። አለበለዚያ የአምልኮቱ ሁኔታ ይበላሻል።

### በ) ድምፁን መድረክ ላይ ከወጣ በኋላ መፈተን

ይህ ሁሉ ቀደም ሲል እንደተናገርነው ወደ መድረክ ከመውጣት በፊት መደረግ ያለበት ነገር ነው።

### ተ) አዲስ መዝሙሮች ማብዛት


ቀደም ብለን ከአጃቢዎች ከመዘምራን ቡድኑና ከሙዚቀኞቹ ጋር አዲስ መዝሙር የተለማመድን ከሆነ ከእነዚያ መዝሙር ውስጥ ሳይበዛ አንድ ወይም ሁለቱን ለጉባዔው በማስተማር እነዚያን መዝሙሮች ለአምልኮ መጠቀም ይቻላል። ነገር ግን አንድ መሪ መድረክ ላይ ቆሞ ለማስተማር የሚፈልጋቸው አዳዲሶች መዝሙሮች ብቻ ከሆኑ፤ ጊዜው የአምልኮ በመሆን ፈንታ የመዝሙር ጥናት ጊዜ ይሆናል።

## የአምልኮ ስብሰባ መሪ ቡድን (team)

የአንድ አምልኮ ስብሰባ የሚመራው በአንድ የስብሰባ መሪ ቢሆንም ሙዚቀኛው ወይም ኦርኬስትራው፣ አጃቢ ዘማሪዎች፣ መጋቢው ሌሎችም ሁሉ የስብሰባው አመራር ተካፋዮች መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል። በተለይ በአሁኑ ዘመን በፔንቴኮስታል አብያተ ክርስቲያናት በቡድን አምልኮን መምራት የተለመደ ነው። በአጠቃላይ የአምልኮ መሪ ቡድን የምንላቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።


ሀ) የአምልኮ ስብሰባ መሪ ለ) ሙዚቀኛው/ኦርኬስትራው ሐ) አጃቢ መዘምራን (እነዚሁም በመድረክ ላይ ስለሚገኙ አንዳንድ ጊዜ በመዝሙር ያጅባሉ) መ) መጋቢው ሠ) ሌሎችም (በአንዳንድ የፔንቴኮስታል ስብሰ ባዎች አሸብሻቢዎች (dancers) እና የመሳሰሉትም ይጨመሩበታል)።

<u>የሚከተለው ቻርት ይህንኑ ያሳያል</u>




© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

እነዚህ ሁሉ ከእግዚአብሔር በታች ስለሆኑ ትክክለኛ ምንነታቸው ሊገለጽ የሚችለው በተገለበጠ ባለሦስት መስ መር ስዕል (Triangle) ነው። ስለዚህ ከዚህ ቀጥሎ የተገለበጠ ባለ ሶስት ማእዘን ቅርጽን (Triangle) በአእምሮ አችን በመሳል የአምልኮ ቡድን ቅደም ተከተል እንገልጻለን።



በሥዕሉ መጀመሪያ መገኘት ያለበት እግዚአብሔርን ነው። ምክንያቱም የመጨረሻ ሥልጣን ያለው በእግዚአብ ሔር እጅ ነው። ስለሆነም ፓስተሩ በዕለቱ ለሚሰጠው መልእክት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ይፈልጋል ይከተላልም። የስብሰባው መሪም እንደ ፓስተሩ እግዚአብሔር በመንፈሱ እንዲመራውና የአምልኮውን አቅጣጫ እንዲያሳየው ፈቃዱን መፈለግ አለበት። የቀሩትም የአምልኮ ስብሰባ መሪ ቡድኖች አይን እግዚአብሔር ላይ መሆን አለበት።

## በቡድን የሚመራ አምልኮ የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል።

### ሀ. መረዳዳት

በቡድን አገልግሎት ውስጥ መረዳዳትና መደጋገፍ አለ። ከቡድኑ ውስጥ አንዱ ቢደክም ወይም የድምጽም ሆነ የሌላ አይነት ችግር ቢያጋጥመው በሌሎቹ የቡድኑ አባላት ይሸፈናል። የደበረውና የደከመውም የሌሎቹ እርዳታ ቀስ በቀስ እንዲሻለውና እንዲበረታ ያደረገዋል። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ የቡድን አባል ድካም ጉባኤው እንዳይበደልና አምልኮውም ያለምንም መደናቀፍ እንዲካሄድ ይረዳል።

### ለ. ኃይልና ብርታት (Synergy)

አንድ ሰው 1,000 በያባርር ሁለት ሰው 10,000 እንደሚያባርር (ዘዳግም 32፥10) በመናገር መጽሐፍ ቅዱስ የሕብረትን ጥቅም ያስረዳል።

## የአምልኮ መሪ ቡድን አባላት ድርሻ

### ሀ) የመጋቢው ድርሻ

ስለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ሁኔታ በእግዚአብሔር ፊት ኃላፊነት ያለበትና ተጠያቂው መጋቢው ነው። ስለሆነም የአምልኮው ቡድን በቀጥታ በመጋቢው አመራር ስር ነው። ለአምልኮ ቡድኑ ራእይ (vision) እና ቅስቀሳ (motivation) መስጠት ያለበትና ለእያንዳንዱ ስብሰባ መመሪያና አቅጣጫ የሚሰጠውም መጋቢው ነው። መጋቢው በየጥቃቅኑ ሁኔታ ሁሉ እጁን ማስገባት ባያስፈልገውም በእለቱ መደረግ ስለሚገባቸው ነገሮች ቡደኑ መመሪያ የሚያገኘው ከመጋቢው ነው። መጋቢው በየቡድኑ ልምምድ ላይ መገኘት ባያስፈልገውም ለየቡደኑ በተለያዩ አርእስቶች ላይ መመሪያ፣ ትምህርትና ስልጠና የመስጠት ኃላፊነት አለበት።

ለምሳሌ አንድ እንግዳ ተናጋሪ ወይም ዘማሪ ተጋብዞ ቢመጣና በአገልግሎቱ አከራካሪ ወይም ግልጽ ያልሆኑ ጥያቄዎች ቢነሱ የአምልኮ መሪ ቡድን አባላት በጉዳዩ ከመጋቢው ጋር በመነጋገር የመጋቢውን መልስ (response) ማወቅና በዚያውም መመራት አለባቸው።

### ለ) የአምልኮ መሪው ድርሻ

ሙዚቀኛውን/ኦርኬስትራውንና ሌሎቹንም አጃቢ መዘምራንን የሚመራው የስብሰባው መሪ ነው። ስለዚህ ሌሎቹ የቡድኑ አባላት ሁሉ እርሱን መከተል ይገባቸዋል። ከመዝሙር ምርጫ ጀምሮ መዝሙሮቹን የማቆምም ሆነ የመቀጠል ወይም ሙዚቃውን የመለወጥ ሁሉ ኃላፊነት ያለው መሪ ብቻ ነው። ስለዚህ አጃቢ



© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

ዘማሪዎችም ሆኑ ሙዚቃ ተጫዋቹ መሪውን በጥንቃቄ መከተል ይገባቸዋል።

### ሐ) የአጃቢ መዘምራን ድርሻ

አጃቢ መዘምራን መሪውን ለማገዝና እምልኮውን ለማድመቅ የተመደቡ ናቸው። ስለዚህ በቅድሚያ ራሳቸው አምላኪዎች መሆን ሲገባቸው ከአለባበስ ጀምሮ እስካሁን የዘረዘርናቸውን ጨምሮ የመድረክ መመሪያዎችን በሙሉ መከተል ይገባቸዋል። በዚህ ሁሉ ላይ ግን የስበሰባ መሪውን መከተል እንዳለባቸው መዘንጋት የለባቸውም።

### መ) የሙዚቀኛው/የኦርኬስትራው ድርሻ

ሙዚቃ ዋና የአምልኮ መሳሪያ በመሆኑ በአምልኮ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው። ነገር ግን ሙዚቀኞች የአምልኮ መሪዎች አይደሉም። የስበሰባው መሪ ብዙ የሙዚቃ ችሎታ ባይኖረው እንኳን መሪውን መከተል ይገባቸዋል።

### ሠ) የጉባኤው ድርሻ

ጉባኤው መሪውን የመከተል ኃላፊነት አለበት። ነገር ግን ይህ ኃላፊነት በመሪው አመራር የሚወሰን ነው። በአንዳንድ ስብሰባዎች አንዳንድ የጉባኤው አባላት ጉባኤውን ለመምራት ይሞክራሉ። ለምሳሌ እነርሱ የሚዘምሩትን መዝሙር ጉባኤውና መሪው እንዲከተላቸው ልዩ ጥረት ያደርጋሉ። ይህ ሁሉ ስርአት አለመከተል ነው።የስብሰባው አቅጣጫ ከመንፈስ ቅዱስ ቀጥሎ በመሪው የሚመራ መሆኑን መገንዘብ የጉባኤው ኃላፊነት ነው። ስለዚህ ጉባኤው መሪውን በአግባብ ሊከተል ይገባል እንጂ አንዳንድ የጉባኤው አባላት በፊለ ጉት መንገድ ጉባኤውን እንዲቆጣጠሩ ማድረግ የለበትም።

## በስብሰባው መሪና በመጋቢው መካከል ሊኖር የሚገባ ግንኙነት

ለአምልኮ በምንሰበሰብበት ጊዜ ሁሉም የራሱ የሆነ ድርሻና ቦታ እንዳለው ማወቅ ይገባል። ይህንንም ኃላፊነት ለመወጣት በሁሉም መካከል ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ይገባል። ከነዚህ አስፈላጊ ግንኙነቶች አንዱ በመሪውና በመጋቢው መካከል የሚደረገው ግንኙነት ነው። በተለይ መከባበር (respect) መተሳሰብ መነጋገር (communication) አስፈላጊ ነው።

የስብሰባው መሪ ከመጋቢው ጋር ያለ መስማማት ካለው በንዴትና በክፉ መንፈስ በጉባኤውና በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም አይገባውም። ይህ የጌታን ስራ መበደል ይሆናል። መጋቢውም ከስብሰባው መሪ ጋር ያለመስማማት ቢኖረው ሁኔታውን ተወያይቶ ሳያስወግድአገልግሎት ለሁሉም ለማዳረስ በማለት ብቻ የስብሰባ መሪው በጉባኤውና በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ እንዲያገለግል ማድረግ አይገባውም።

የሙዚቀኛውና የስብሰባ መሪው ግንኙነት

- መግባባት
- መረዳዳት
- መደጋገፍ
- መከባበር

ስራቸውን በሚገባ ማካሄድ እንዲችሉ በመካከላቸው የኃላፊነት ልዩነት እንጂ የአንዱ አገልግሎት ከሌላው የሚበልጥ ወይም የሚያንስ አለመሆኑን መረዳት ይገባቸዋል።

ሙዚቀኛውና የስብሰባ መሪው አብረው በመጸለይና አብሮም በመለማመድ መረዳዳትና አገልግሎታቸውንም የበለጠ ማሻሻል ይችላሉ።

© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

## ከአምልኮ ቡድን በአጠቃላይ የሚጠበቁ

**ሀ) በሕብረት ማምለክ/መጸለይ**

በጋራ የሚኖራቸውን የልምምድ ጊዜ አብሮ የመጸለይና የማምለኪያ ጊዜ አድረገው መጠቀም ይችላል።

**ለ) መጽሐፍ ቅዱስን አብሮ መማርና ማጥናት**

በተለይም አገልግሎታቸውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የጋራ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሊኖራቸው ይገባል።

**ሐ) መወያየት**

በየጊዜው ስለአምልኮና ስለ አገልግሎታቸው መነጋገርና መወያየት ጠቃሚና የሚገባ ነው።

**መ) ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት መገናኘትና በሕብረት መጸለይ።**

**ሠ) ለሕብረቱና ለሕብረቱ አገልግሎት የተሰጡ መሆንና እርስ በእርስም መተናነጽና አንዱ ሌላውን ማበረታታት**

**ረ) ገንቢና ጠቃሚ እርማት በመስጠትና በመቀበል።**

**ሰ) እርስ በእርስ ለመማማር (teachable) መሆን**

## የአምልኮ ስብሰባን ማቀድ (Planning)

ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት በመታዘዝ (sensitive ከመሆን) ጋር ለእያንዳንዱ ስብሰባ መሪው ጥሩ የሆነ ፕላን ሊኖረው ይገባል። ይኸውም፥

**ሀ) መዝሙሮችን መምረጥ**

**ለ) ጥሩ የስብሰባ አጀማመር ማቀድ**

የስብሰባ አጀማመሩ ሁሉን ነገር ሊያሳምር ወይም ሊያበላሽ ስለሚችል የስብሰባው አጀማመር ጥሩ እንዲሆን መሪው በጥንቃቄ ፕላንማድረግ ይገባዋል።

**ሐ) መዝሙሩ ዓይነት (variety) ያለው እንዲሆን ማድረግ።**

ማለትም -

1) ወንዶች ብቻ
2) ሴቶች ብቻ
3) በሙዚቃ ብቻ (በተለይ የመባ፣ የአስራትና የጸሎት ጊዜ)
4) አንዳንዴ ያለ ሙዚቃ
5) በለሆሳስ ወይም በዝቅተኛ ድምጽ
6) ጉባኤው ተከፋፍሎ እየተከታተል እንዲዘምር ማድረግና ይህንን የመሳሰሉ ሌሎችንም የአዘማመር ዘዴዎችን ያጠቃልላል።



© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS WWW.ECFCHOUSTON.ORG

## ማጠቃለያ

ለጌታ ለኢየሱስ የምናደርጋቸውን አገልግሎቶች ሁሉ ከልብና በአለን ችሎታና ኃይል ሁሉ ልናደርገው ይገባል። አገልግሎት ክቡር ነው።  አገልግሎታችንን እንደ ቀላል ነገር መቁጠር የለብንም።  የተሰጠንን አገልግሎት ስናከብር ጌታንም እናከብራለን።  ለጌታ የምንሰጠውን አገልግሎት ሊያሻሽልልን የሚችለውን እድል ሁሉ መጠቀም አለብን።

**ይህ የስልጠና ትምህርት ለሁላችንም የመጀመሪያው እንጂ<br>የመጨረሻው መሆን አይገባውም።**

© 2006 ETHIOPIAN CHRISTIANS FELLOWSHIP CHURCH, HOUSTON, TEXAS   WWW.ECFCHOUSTON.ORG